የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
አዲስ አበባ/ADDIS ABABA

ኢሲማዳ/ዳ/47/2021

ሰኔ 28 ቀን 2014

ለሁሉም ባንኮች
ለሁሉም አነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት
ለሁሉም የኢንሹራንስ ኩባንያዎች
ለኢትዮ ስዊች አ.ማ
አዲስ አበባ፡፡

ጉዳዩ፣ **በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የተዘጋጁትን ስታንዳርዶችና ማዕቀፎችን ስለማሳወቅ፡፡**

የፋይናንስ ተቋማት ከፍተኛ መጠን ያላቸውን የደንበኞችን መረጃዎች የያዙ እና ለሳይበር ጥቃት ዋና ኢላማ በመሆናቸው ተቋማቱ የሳይበር ጥቃት የመጠበቅ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ ተገቢው የሳይበር ደህንነት ቁጥጥር ከሌለ የደንበኞቻቸውን የግል መለያ መረጃዎች ለሳይበር ጥቃት ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡ ይህም የፋይናንስ ተቋማት የሳይበር ደህንነት ተገዢነትን ደረጃ ያመለክታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ጥሰት በሚደርስበት ጊዜ ከፍተኛ የገንዘብ ቀውስ እና የሰርቪስ መቋረጥ ያስከትላል፡፡

በፋይናንሽያል አገልግሎት ኢንዱስትሪ ውስጥ የሳይበር ደህንነት ተገዢነትን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ካለው የሳይበር ጥቃት አሳሳቢነት አንፃር አንድ እርምጃ ወደፊት ቀድመን የሳይበር ጥቃት ለመከላከል ዝግጁ መሆን አለብን፡፡ በመሆኑም የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የሀገሪቱ ቁልፍ መሠረታዊ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ለመጠበቅ ያወጣቸውን ስታንዳርዶችና ማዕቀፎች መተግበር የሳይበር ደህንነት ስጋት ለመቀነስና ለመከላከል ያስችላል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ 23 NATIONAL BANK OF ETHIOPIA

አድራሻ: ሱዳን ጎዳና: Address: Sudan Street | ፖ.ሣ.ቁ.: P. O. Box: 5550/2048 | ፋክስ: Fax No.: +251-11-551-4588 | ስልክ ቁጥር: Tel. No.: +251-11-551-7430 | Website: www.http://nbe.gov.et SWIFTCODE - NBETETAA

ይህንን ከግንዛቤ በማስገባት የፋይናንስ ተቋማት የተዘጋጁትን አጋዥ እና አስገዳጅ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች ተግባራዊ በማድረግ የጋራ ሀላፊነታችንን መወጣት አለብን፡፡ በመሆኑም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማዕቀፎች ሁሉም የፋይናንስ ተቋማት በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የወጡትን መመሪያዎች እንዲተገብሩት ያስገድዳል፡፡

ከሠላምታ ጋር

ወንድወሰን ፀጋው
ዳይሬክተር፤ የኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት

አባሪ፣

- የሳይበር ደህንነትን ስታንዳርዶችና ማዕቀፎችን ስለማሳወቅ የኢንፎርሜሽን ደህንነት አስተዳደር ደብዳቤ

ግልባጭ፣

- ለክቡር ገዥ
- ለም/ ገዥ - ኮርፖሬት ሰርቪስ
- ለም/ገዥ - የፋይናንሻል ኢንስቲቲዩሽን ሱፐርቪዥን

በኢ.ፌ.ድ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
FDRE Information Network Security Adminstration
: 251-11-371-71-14 124498 FAX : 251-11-320-40-37

ቀን Date 16/9/2014
ቁጥር No. አመዕሽ/አመ34/ሬ5

በዝርዝሩ ለተመለከቱት

በያሉበት

ጉዳዩ፡- **የሳይበር ደህንነት ስታንዳርዶችና ማዕቀፎችን ስለማሳወቅ**

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሠረት ያደረጉ ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ደህንነትን በማረጋገጥ በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ያላቸውን አስተዋፅዖ ማሳደግ ዓላማው አድርጎ በአዋጅ ቁጥር 808/2006 መሰረት ሃገራዊ የሳይበርና የዲጂታል ሉአላዊነትን ከማረጋገጥ አንፃር በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከነዚህም መካከል የኢንፎርሜሽን እና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ቁልፍ መሰረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሀገራዊ ፖሊሲዎችን፣ የህግ ማዕቀፎችን፣ ስታንዳርዶችን እና ስትራቴጂክ ሰነዶችን ረቂቅ የማዘጋጀት ሲፀድቁ ተግባራዊነታቸውን የመከታተል ኃላፊነት ተጥሎበታል።

በተመሳሳይ አስተዳደሩ በሀገሪቱ የሚገኙ መንግስታዊ እና የግል ተቋማት ሀገራዊ የኢንፎርሜሽን ደህንነት ፖሊሲ እና ስታንዳርድ ማዕቀፎች ተከትለው የራሳቸውን ፖሊሲ እና ስታንዳርድ ቀርፀው ስራ ላይ እንዲያውሉ ድጋፍ የመስጠትና አፈፃፀማቸውን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት። ይህንንም የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት አስተዳደሩ ባለፉት ዓመታት የተለያዩ ማዕቀፎች እንዲወጡ በማድረግ የሀገሪቱን የሳይበር ደህንነት ለማስጠበቅ በፖሊሲና በአሰራር ስርዓት ተቋማት እንዲተገብሩት ጥረት ቢደረግም በርካታ መቆራረጦችና የአፈፃፀም ክፍተቶች እንዳሉ በጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት አስተዳደሩ ከምን ጊዜውም በላይ በሀገራችን እየጨመረ የመጣውን የሳበር ደህንነት ስጋት ለመቀነስና ለመከላከል የሚያስችሉ የዘርፉን የቴክኖሎጂ ባለቤትነትን ለማጠናከር፣ የበቁ የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችን ለማፍራት እና አስፈላጊ የአሰራር ስርዓቶችን ለመዘርጋት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

ከነዚህም ተግባራት መካከል በዋናነት የሀገሪቱ ቁልፍ ኢንፎርሜሽንና ኮምፒውተርን መሰረት ያደረጉ ልማቶችን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችሉ አጋዥ እና አስገዳጅ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎችን ማዘጋጀት ነው። በዚህም መሰረት አስተዳደሩ የመንግስትና የግል ተቋማትን የሳይበር ደህንነት በማስጠበቅና ድጋፍ በማድረግ ረገድ የተጣለበትን ሀገራዊ ኃላፊነት ለመወጣት ያስችለው ዘንድ አስፈላጊውን ሂደቶች ሁሉ አልፈው የሚከተሉት ማዕቀፎች ተዘጋጅተዋል፡፡

በኢፌዴሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
FDRE Information Network Security Adminstration

ቀን. Date _____
ቁጥር. No. _____

: 251-11-371-71-14 124498 FAX : 251-11-320-40-37

1) ደህንነቱ የተጠበቀ የድህረ ገፅ አመራር ስታንዳርድ (Secure Website Management Standard)
2) ደህንነቱ የተጠበቀ የሶፍትዌር ልማት እና አመራር ስታንዳርድ (Secure Software Development and Management Standard)
3) ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ማዕቀፍ ልማት ስነ-ዘዴ (National Cyber Security Framework Development Methdology)
4) የሳይበር ደህንነት ስጋት ትንተና ማዕቀፍ (Cyber Security Risk Assessment Framework)
5) የሳይበር ደህንነት አደረጃጀት እና የሥራ መደብ ማዕቀፍ (Institutional cyber Security internal unit)
6) ሀገራዊ የሳይበር ደህንነት ዳሰሳ ሪፖረት (National cyber Security assessment report)

በአስተዳደሩ ድህረ ገፅ ላይ እንዲጫኑ ተደርጓል። በመሆኑም በተቋሙ ድህረ-ገጽ www.insa.gov.et ላይ በመግባት ሰነዶች የሚለውን አማራጭ በመክፈት ዝግጁ የተደረጉትን የሳይበር ደህንነት ማዕቀፎች እንዲተገበሩ በማድረግ የተቋማችሁን የሳይበር ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊው ሁሉ እንዲፈፀም እየጠየቅን፤ ለተጨማሪ ማብራሪያ እና እገዛ አቶ ሃኒባል ለማ ስ.ቁ 0911-02-22-97 ወይም 0904-04-86-58 ወይም በEmail፡hanibal@insa.gov.et ማግኘት የሚቻል መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ፡-
- ለኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት
- ለኢፌዲሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢፌዲሪ ፕላንና ልማት ሚኒስቴር

አዲስ አበባ